# <u>ድንቁም ሰፊ ግንባር--ክህደት በሽፍንፍን ሲውገረገር</u>

“ ሽፋፍቶቹም ወደ ላይ የሚያዩ ትውልድ አለ ::
ድሆችን ከምድር ላይ፤ችግረኞችንም ከሰው
መካከል ያጠፋና ይጨርስ ዘንድ
ጥርሶቹ ሰይፍ፤መንጋጎቹም ካራ የሆኑ ትውልድ አለ :::
(መጽሀፈ ምሳሌ ተግሣጽ/ምዕራፍ 30/)

ያ ለድሀ ወገኑ ሊሞት ሊሰዋ ቆርጦ የተነሳውንና ደሙን ያፈሰሰውን ትውልድ የሚተኩ ሰው በላ ጥርሳቸው የተሳለ ባንዳዎችና ከሀዲዎች ዛሬ ፈልተውብናል:: ሆዳቸው ከጥሬ ወፍጮ በላይ የጠነ ከረ :: ህሊናቸው በድን የሆነ፤ የጫጫ የሞተ :: ዛሬ ለአረመኔው ወያኔ በስልት ለማደር ተነስተው ሰፊ ግንባር ይመስረት የሚሉን ከዚህ ቢፈረጁ ስህተት የለውም::

በቅድሚያ የሰለቸ ምሳሌን መድገሙ የግድ ነውና ድር ቢያብር አንበሳ ያስር መሆኑን የሚፃረር ብዙ ሰው ሊኖር አይችልም:: ድር ሲያብር ግን ድር በመሆኑ እንጂ ድር፤ክር፤ቃጫ፤ ወዘተ ሆኖ ተዘበራርቆ አይደለም:: ድር ሲያብርም ግቡን አውቆ ነው--አንበሳን ለማሰር እንጂ አንዱ ልሰር ሲል ሌላው ደግሞ ጌጥ ልሁንለት ካለ የሚታሰር አንበሳ አይኖርም፤እንኳን አንበሳ ጠቦትም አትሽ በብም:: በሀገራችን የአንድነት ግንባር ጥረቶች ብዙ ጊዜ ታይተው፤ውጤትም አሳይተው ግን የመጨረሻ ግባቸውን ሳይመቱ አልፈዋል:: ለምን ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው--ከስህተት ተምሮ ለመታረምና የተሻለውን በሚቀጥለው ለመስራት:: ትላንት ህብረት ህብረት ያሉን ሁሉ ዛሬ በወያኔ ፓርላማ ደፋ ቀና የሚሉ ኢምንቶች መሆናቸውን መካድ አንችልም:: ማንዴላ የተባለው ም ዓይንአውጣ ምንደኛ ሆኖ ጭፍሮቹን አሳፍሯል:: መብል ወዳጆች ከቶም የማይጠግቡ ውሾች ናቸው እንደተባለው ሁሉ ( ትንቢተ ኢሳይያስ፤56/11) ሆዳቸውን ያስቀደሙ ግብዞች የህብረት ጥረትን ደግመው ደጋግመው አደናቀፉት:: የልባቸውን በልባቸው ይዘው ሕዝብንም ማደናገር ልማዳቸው ነውናም በዴሞክራሲ ስም አምባገነንትን፤ በህብረት ስም ክፍፍልን፤ በሕዝብ ስም የግል ጥቅምን በማስቀደም ትግላችንን ሲጎዱ ቆዩ:: ዛሬ ሰፊ ግንባር ይመስረት ወይም መመስረት አለበት ብለው ፀረ ወያኔውን ትግል ሊያደናቅፉና ከትቢያ ሊደባልቁ የተነሱትን መሰሪዎች ማንነት አስቀድሞ ማወቅና ጥረታቸውንም ማክሸፍ የሁሉ ዜጋ ግዳጅ ሊሆን ይገባዋል::

የዚህ አስመሳይና አጉል ጥሪ አባወራዎች ለመሆኑ እነማን ናቸው?

-- ሀገር ወዳድ ድርጅቶችንና መሪዎችን ነጋ ጠባ ሲሰድቡና ለማዋረድ በየመድረኩ ሲጥሩ የምንታዘባቸው ፤

-- ድርጅቶችን ደግመው ደጋግመው የካዱ አንጃዎች፤

-- ሕዝብ የጠላውን የአንድ ብሄረሰብ የበላይነት ፖለቲካ በአዲስ መልክ ሊያራምዱ ያቋመጡና ሕዝብን ይቅርታ ያልጠየቁ ወንጀለኞች፤

--ራሳቸውን ድርጅት ቢሉም ምኞት እንጂ ይህን ሀቅ ማድረግ የተሳናቸው ክፍሎች፤

--ሰርጎ ገብና አደናጋሪ ወያኔዎች ናቸው::

በቅርቡ በአንድ ወገንተኛና ከልልተኛ የሆነና የአፍራሽ ቅስቀሳ መዲና የሆነ ፓልቶክ ውስጥ የቀረ ቡትን እንግዶች ማንነት ስናይና ሲለፈፍ የነበረውንም እንደሰማነው ከሆነ ይህ ሰፊ ግንባር ምስረ ታ አንድ ዜጋ በፃፈው ቁምነገር እንደጠቀሰው ከኋላው ጉድ ይዞ መምጣቱን ለመገንዘብ ችለናል: : በደፈናው ሲታይ ግንባር ይመስረት ጥሪ መጥፎ ነው ሊባል አይቻልም:: መጠየቅ ያለበት ግን የእነማን ግንባርና ለምን ግብ የሚለው ነው:: የከፉ አሕዛቦችና ፈሪሳውያን በዋሾ ምላሳቸው የሚጠሩት ግንባር አለመሆኑን ማጣራት ያስፈልጋል:: ሚዛኑና ክብደቱንም ማወቅ ተገቢ ነው:: ወደል ጎረምሳ ቢጨምቃቸው ከነጭላጫቸውና አተላቸው ተደምረው የአራት እጅ ጣት የማይሞ ሉና አልፎም አቅዋማቸው ከሕዝብ ሳይሆን ከሕዝብ ጠላት የሆኑ ስብስቦች ድርጅቶች ነን ብለው ቢመፃደቁ ዋጋ የለውም:: ጥቂት አሻሮ ይዞ ካለው መጠጋት ይሆናል እንጂ ለትግሉም ምንም ጥቅም ሊሰጡ እንደማይችሉ ከዚህ ቀደም የታየና የተረጋገጠ ጉዳይ ነው:: ወደ ተራራ ወጣሁ ያለ ሁሉ አሥርቱ ቃላትን ተቀብሎ አይመለስም::

ዛሬ በኢትዮጵያ ዋናው ትግል የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ፣ ለመጣልና ለአንዴም ለሁሌም ለመቅበር የተነሳ መሆን አለበት:: ወያኔን በግፉና በሀገር አጥፊ ስርዓቱ ለማጀብ መነሳት ከሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ተፃራሪ ነው:: ይህ ነው መሰረታዊና የመነሻችን አቅዋም:: እነ ገብሩ አስራትና ስዬ አብርሀና ሌሎች መለስን አስወገድው የወያኔን የበላይነትና አገዛዝ ለመቀጠል ፈላጊዎች ናቸው:: ትላንት በሕዝብ ላይ ለፈፀሙት ወንጀል ይቅርታ ሲጠይቁም አልተሰሙም:: በስልጣን ሳሉ አስረው ስላጠፏቸው ወገኖች የተነፈሱት የለም:: ከሀዲዎች ይህ ሀቅ ባያንቃቸውም ለሀቀኛ ዜጎች ግን የሚያም ነው::ሌሎች ለወያኔ ያደሩ ክፍሎችም የአገዛዙን መንኮታኮት አይፈልጉም-- የሕዝብን ቁጣ ይፈራሉና ነው:: የዚህም የዚያ አንጃዎች ደግሞ ዕድል አግኝተው በተራቸው የመለስን ጫማ ሊስሙ ፈልገዋል:: የበደኖና አሶሳ አስጨፍጫፊዎች ደግሞ ዛሬም ለሕዝብና ለሀገር አንድነት ቀና አመለካከት የላቸውም:: ሊሰባሰቡ የተነሱት እነዚህ ናቸው:: የህብረታቸው ወይም ሰፊ ግንባራቸው ግብም ሰብስብ ብለው ጎንበስ ለማለት ነው--ለወያኔ:: በምርጫ መሳተፍ ፣ የሰለጠነ ፖለቲካ መከተል፣ ከጥላቻ መስመር መራቅ ብለው ይህን የባንዳነት አቅዋም አሽሞን ሙነው ያቀርቡታል:: የሰፊ ግንባራቸው ዓላማ ፀረ ወያኔ ሳይሆን ወያኔን እንደ ስርዓትና አገዛዝ ማጀብ ነው ማለት ነው:: ይህ አቅዋም የከሀዲና የዘመናዊ ባንዳ፣ የአስከፊ አንጃነት ነፀብራቅ ነው ካልተባለስ ምን ሊባል ነው?

ዛሬ ጎራ በሚጋበ ለይቷል፣ተለይቷል::በቃላት ማደናገርና ሕዝብን ማታለል አይቻልም:: የቱ አዋቂ የቱ ደግሞ ዜሮ ቀፎ እንደሆነ፣ የቱ የሕዝብ አለኝታ የቱ ደግሞ የሆዱ ጠበቃ እንደሆ ነ ታውቋል:: ክህደት የለመደባቸውና ለወያኔም ስርዓት የብዕር ኩሊና ሀፍረተ ቢስ መጋዣ የሆኑት ታውቀዋል::ግንባር ስለተባለ ብቻ እሰየው ብሎ የሚቧርቅ የለም:: ለሕዝብ ቆመናል ወይም መስዋዕት ልንሆን ተነስተናል ስላሉ ብቻ በድፍኑ የሚያምን ጥቂት ነው:: ሕዝብ በተግባር ይፈትናል፣ ይታዘባል፣ይለያል፣ለይቷል:: ሕዝብ ባለፈው የማሚያ ምርጫ አልተሳተፈም:: የወያኔ

ምርጫ የአረመኔ ጨዋታ መሆኑን ደሙን አፍሶ ተረድቷልና ነገ ምርጫ ልንገባልህ ነው የሚሉት ን ይተፋባቸዋል እንጂ አያከብራቸውም። እነ ፀጋዬ ገብረ መድህንን ያጠፉትን፣ ስንቱን ንፁህ ዜጋ የመተሩትን፣ ጦርነት እንሰራባችኋለን ብለው የፎከሩትን፣አማራን ከምድር ገፅ እናጠፋለን ብለው የደነፉትን፣ ወዘተ ቢያንስ ይቅርታ ሳይጠይቁ፣ቁጭትና ሀዘኔታን ሳያስሙ ወዳጅ ብሎ ሊያቅፋቸውና ሰለባ ሊሆንላቸው መጠበቅ የለበትም። ሕዝብን መናቅ ይሆናል ደግሞ ደጋግሞ ሕዝብን ለማታለል ማለሙ። አንጃው ከኢሕአፓ የተለየው የወያኔን የበላይነት ተቀብለን እሱው በሚፈቅድልን መሰረት እንቀሳቀስ በማለቱ ነው። የቅንጅትም ክፍፍል ይህን የትግል ምርጫን የተመለከተም መሆኑ የሚሳት አይደለም። ነገ ማን ይሁን ማን ወያኔን ለማጀብ ከተነሳ ሕዝብ አንቅሮ ይተፋዋል። ወያኔን በትጥቅ ትግል እንፋለመዋለን ካሉ በኋላ ትጥቅ ትግልን አውግዘው ከወያኔ ጋር ላንፋታ ተጋባን የሚሉትን ለማቀፍ መነሳታቸው ራሳቸውን የሚያስጠይቃቸውና አባይ የሚያሰኛቸው ነው።

ሰፊ ግንባር ምስረታ? የእነማን ግንባር? ለምን ግብ? የዚህ መልሱ ሰሞኑን የተጀመረው ጫጫታ በመሰረቱ በትግላችን ላይ ሌላ የተሸረበ ሴራ መሆኑን የሚያሳይ ነው። እነማን ሊተቃቀፉ ደፋ ቀና እንደሚሉ ሲታይና አቅዋማቸውም " ፈጠን በል ጃል፣ ወንበር እንዳያልቅ እንዳንጃጃል" ዓይነት ጥሪ ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩ ግልፅ ይሆናል። እጅ የሰጡና ለወያኔ ሊያድሩ የተነሱ የቀቢፀ ተሰፋ ና የስልጣን ጥም ሰለባዎች በትግሉ ላይ ተነስተዋል፣ ሊያብሩ ሊተባበሩና ትግላችንን ሊቀብሩ ተነስተዋል። ለወያኔ መስገዱን በተመለከተ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው ። ወያኔ ተጫውቶባ ቸው እንደሚጥላቸው ግን ግልፅ ጉዳይ ነው።ሀገር ወዳዱ ሁሉ ግን ይህን ሴራ ለማክሸፍ ነቅቶ መጠበቅና መነሳት አለበት። የባንዳ ሰፊ ግንባር ስፋቱ በሆዱና በፍርሀቱ ልክ ነው። እውነተኛ ሀገር ወዳድ ሀይሎች ደግሞ በተቃራኒው ትብበራቸውን ማጠናከር አለባቸው--ፀረ ሕዝቡን የወያኔን አገዛዝ ለመጣልና ለማስወገድ።

ጥርሳቸው ሰይፍ፣መንገጋቸው ካራና ምላሳቸው መርዝ ከሆኑት፣ክቡር ስምና ታሪክን ከሚያከረፉት እንራቅ!!!

ተድላ ሙሉጌታ